**ለሁለተኛው የማርክ መስጫ ወቅት እና ከዚያም ባሻገር የሥርዓተ ትምህርትና የትምህርት አሰጣጥ ማስተካከያዎች**

ዲሰምበር 3፣ [ስለ አንደኛው የማርክ መስጫ ወቅት የተማሪዎች የትምህርት አፈጻጸም ውጤት]() ወቅታዊ መረጃ ለትምህርት ቦርድ ቀርቧል። ይህም በመካከለኛ እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ብዙ ተማሪዎች የመውደቅ ሁኔታ የጨመረ መሆኑን ያመለክታል። ስለ ቨርቹወል ትምህርት የተማሪዎችን የትምህርት እርምጃ/እድገት በተመለከተ ከተማሪዎች፣ ከሠራተኞች እና ከወላጆች ለተገኘው ግብረ መልስ ምላሽ ለመስጠት ሲባል የተማሪ/የመምህር ተሞክሮን ለማሻሻል፣ የተማሪዎችን ደህንነት ለማዳበር እና ተማሪዎች በስርአተ ትምህርቱ ላይ እየተጉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የማስተካከያ ለውጦች እየተደረጉ ናቸው። እነዚህ ማስተካከያዎች የሚደረጉትም ስለ ቨርቹወል ትምህርት መርሃግብር፣ የስርዓተ ትምህርቱ ይዘት እና የጥድፊያ ሁኔታ፣ የተማሪ የኮርስ ብዛት እና የስራ ጫና፣ እንዲሁም የመመዘኛ ፈተና ብዛት እና ድግግሞሽን በተመለከተ ለተሰጡት ግብረመልሶች መፍትሔ ለመስጠት ነው። ለሁለተኛው የማርክ መስጫ ወቅት የተደረጉ ማስተካከያዎች የሚከተሉት ናቸው፦

- የስርዓተ ትምህርት ይዘት እና የጥድፊያ ሁኔታን በቀጣይነት መገምገም፣ እና መሸፈን ያለባቸውን የትምህርቶች ብዛት እና ይዘት መቀነስ
- በዊንተር የሚካሄደው MAP አድሚንስትሬሽን ከአሁን በኋላ የግዴታ ሳይሆን በምርጫ ፍላጎት የሚሰጥ ይሆናል
- የረቡዕ ቀናት የኤለመንተሪ መርሃግብር ጋር በተያያዘ የተደረጉ ማስተካከያዎች
- የሁለተኛ ደረጃ ሂሣብ፣ እንግሊዝኛ እና ESOL ተፈላጊ የሆኑ የማሻሻል ርምጃ ማጣራት ቅነሳ
- በሁለተኛ ደረጃ የውጤት አሰጣጥ እና ሪፖርት ማድረጊያ መመሪያ ላይ የተደረጉ ማስተካከያዎች የሚከተሉትን ያካትታል፦
    - ለዲስትሪክት ምዘናዎች አስፈላጊ የሆነውን 10% የውጤት አሰጣጥ መደብ/ካተጎሪ ማስወገድ (ስለማሻሻል እርምጃ ማጣሪያ)
    - አስተያየት የተሰጠባቸው በርካታ ውጤት የተሰጠባቸውን የቤትሥራዎች መቀነስ
    - ለተማሪዎች የተሰጣቸውን የማጠናቀቂያ ጊዜና ቀነ ገደቦችን እንደሁኔታው ተጨማሪ ጊዜ መስጠት
    - ከዜሮ ይልቅ “E” ውጤት ስለመተግበር የ "50% ደንብ" የበለጠ ግልጽ የሆነ መመሪያ ማስቀመጥ።
- ለመምህራን እና ለአስተዳዳሪዎች የሙያ ትምህርትና የትምህርት ቤት ድጋፍ በስፋት ማከናወን
- በቀጥታ ተማሪዎችን ለመደገፍ የትምህርት ቤት ደህንነት ቡድኖችን ማሰማራት

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በወረርሽኙ ምክንያት እና በቨርቹወል ትምህርት ወቅት የተቀናነሱ የትምህርት ጊዜዎችን ተጨማሪ የማስተማሪያ ጊዜ በመስጠት ለማካካስ ተጨማሪ የመማሪያ ጊዜ እቅዶችን ማዘጋጀቱን ይቀጥላል፣ ይህም የማስጠናት፣ የቅዳሜ ፕሮግራሞች፣ የሠመር ትምህርት እና ለተራዘመ ጊዜ የሚቆይ የስርዓተ ትምህርት እቅድን ያካትታል። እንደ አስፈላጊነቱ በሥርዓተ ትምህርት ላይ በየጊዜው ማስተካከያዎች ይደረጋሉ።

በሁለተኛው መንፈቀ ዓመት ምን ማሻሻል እንደሚቻል ለማወቅ በሚደረግ ጥረት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መርሃግብር ገጽታዎች ግምገማ እየተደረገ ነው። ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በመከታተል ለመመረቅ ተፈላጊ ተግባሮችን በማከናወን ላይ መሆናቸውን እና ለወደፊት የኮርስ ሥራ መዘጋጀታቸውን በማረጋገጥ አጠቃላይ የኮርስ ሥራ ጫናውን ለመቀነስ የሚያስችሉ ዕድሎች ይሰጣቸዋል። በተጨማሪም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የኮሌጅ ቦርድ እና ዓለም አቀፍ ባከሎሪየት (International Baccalaureate) ከመሳሰሉ የውጭ ድርጅቶች ጋር ዓለም አቀፋዊ የኮቪድ-19 ን ተጽዕኖ የሚከታተሉ እንደመሆናቸው መጠን በቅርበት አብሮ በመሥራት ስለ ግንቦት 2021 ፈተናዎች ቅርጽና ይዘት ላይ ማስተካከያ የሚደረግ ይሆናል። በሁለተኛው ሰሚስተር ላይ ስለሚደረጉት ለውጦች ተጨማሪ መረጃ በጥር ወር ይገለጻል።

***ሥርዓት አቀፍ የፀረ-ዘረኝነት ኦዲት ወቅታዊ መግለጫ***

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለሁሉም ተማሪዎች እኩል፣ ጠንካራ እና ጠቃሚ ትምህርት ለመስጠት በትጋት እየሠራ ይገኛል። ኖቬምበር 10 የቀረበውን ሲስተም አቀፍ የፀረ-ዘረኝነት ኦዲት ረቂቅ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ አጽድቋል። የኦዲቱ ዋና ዋና ነጥቦች ከዚህ በታች ቀርበዋል።

**በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩል (MCPS) የፀረ ዘረኝነት ኦዲት፡-**
የፀረ-ዘረኝነት ኦዲት የዘረኝነት አድልዎ እና ዝንባሌ በእያንዳንዱ ተማሪ የትምህርት እና ማኅበራዊ ደህንነት ተደራሽነት ላይ ተጽዕኖ እንደማያሳድር ሥርዓት-አቀፍ ተግባሮችንና ፖሊሲዎችን ለመመርመር ዕድል ይሰጣል። ኦዲት ፖሊሲዎችንና አሰራሮችን ለመተንተን እና ዘር፣ ጾታ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ፣ ወዘተ ሳይለይ ለሁሉም ተማሪዎች እንዴት እንደሚሰራ ለመገምገም አስፈላጊ እድል ነው።

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እርምጃ ለመውሰድ ዝግጁ ነው**
በትምህርት ቤት መድልዎ የደረሰባቸው ተማሪዎች ስለ ትምህርት ቤት አሉታዊ አመለካከት እና ዝቅተኛ የመማር ፍላጎት እና አነስተኛ ውጤት እንደሚኖራቸው እንዲሁም ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጥሎ የመውጣት ከፍተኛ ስጋቶች እንደሚኖርባቸው በደንብ ይታወቃል። የፀረ-ዘረኝነት ሥርዓት ኦዲት ይህንን ችግር ለመቅረፍ የድርጊት መርሐ ግብርን ለማሳወቅ ይረዳል። በውጭ አማካሪ ኤጀንሲ የሚካሄደው ይህ የኦዲት ምርመራ እነዚህን ማነቆዎች በመረዳት እና በማስወገድ "ሁሉን ማለት ሁሉንም በሚዛናዊነት ያቀፈ መሆኑን" ማረጋገጥ በሚያስችል ደረጃ የሚካሄድ ወቅታዊ ጉዳይ ነው።

ጃኑወሪ 19፣ የትምህርት ቦርድና የ MCPS ማህበረሰብ ስለ ማህበረሰቡ፣ ስለ ተማሪዎች እና የሠራተኞች ስምሪት የጊዜ ሰሌዳ፣ እንዲሁም ስለ ኦዲት ሂደትና አፈጻጸምን በተመለከተ ዝርዝር መረጃ ያገኛሉ።

**ስለ ፀረ ዘረኝነት ሥርዓት ኦዲት የበለጠ ለማወቅ ይፈልጋሉ?**
ከዚህ በታች ያሉት ሪሶርሶች በኦዲቱ ዙሪያ፣ ዳራ/አመጣጥ፣ እና ዐውድ ተጨማሪ መረጃ ይሰጣሉ። የሥራውን ሒደት እና አቋም በሚመለከት በትምህርት ዓመቱ ውስጥ በኦዲት ድረ-ገጽ ላይ በየጊዜው ወቅታዊ መግለጫ ይሰጣል።

**ተጨማሪ ሪሶርሶች**

ቪድኦ፡- የባለድርሻ አካል ግብረመልስ
የፀረ-መድሎ ኦዲት ድረ ገጽ
ከኖቬምበር 10 የትምህርት ቦርድ በፊት የፀረ-መድሎ ኦዲት ውይይት

ከኦክቶበር 19 የትምህርት ቦርድ በፊት የፀረ-መድሎ ኦዲት ውይይት

**ሱፐር ኢንተንደንት ጃክ ስሚዝ (Superintendent Jack Smith) ዲሰምበር 17 ስለ 2022 የበጀት ዓመት የሥራ ማስኬጃ ባጀት ዕቅድ ያቀርባሉ።**

ሱፐርኢንተንደት ጃክ አር. ስሚዝ ሐሙስ፣ ዲሰምበር 17 የበጀት ዓመት (FY) 2022 የሥራ ማስኬጃ ባጀት እቅድ ለትምህርት ቦርድ እና ለ MCPS ማህበረሰብ ያቀርባሉ። በቪድኦ የሚያቀርቡትን በ MCPS ድረገጽ ላይ ለማየት የሚቻል ሲሆን በ MCPS TV (Comcast Channel 36፣ Verizon Channel 34 እና RCH Channel 89) 7 p.m. ላይ ይተላለፋል።

የባጀት ዓመት (FY) 2022 የሥራ ማስኬጃ ባጀት የተነደፈው፣ የተዋጣለት የትምህርት ቤት አሰራርን ለማስፈን፣ MCPS በየጊዜው የሚያጋጥሙ የውጤታማነት ክፍተቶችን ለመዝጋት ባከናወናቸው ስኬቶች ላይ ለመገንባት እና ሁሉም ተማሪዎች ለ MCPS ኮሌጅ እና ለሙያዊ ሥራ ዝግጁ ሆነው እንዲወጡ ለማድረግ ታስቦ የተዘጋጀ ነው። የ 2022 የሥራ ማስኬጃ ባጀት የቨርቹወል ትምህርት ተፅእኖ ያሳደረባቸው ተማሪዎችን ጨምሮ ለአእምሮ ጤና ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ከማህበረሰብ ተሳትፎ ጋር ስኬታማ የማስተማር ተሞክሮዎችን እና ባህላዊ ተቀባይነት ያለው ሥርዓተ ትምህርትን የማህበረሰብ ሙከራ ት/ቤት ፕሮግራም ተግባራዊ ያደርጋል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ቨርቹወል ትምህርት ተጽእኖ በማሳደሩ ለሚያታግላቸው ተማሪዎች ድጋፎችን ይሰጣል።

## ስለ ፖለቲካ የሥራ መስክ ማወቅ ይፈልጋሉ? "Let's Talk Careers" ሁነት መጪው የውይይት ጊዜ እንዳያመልጥዎት!

የመካከለኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በሙሉ ጥሪ ተደርጎላቸዋል!
በአካባቢ፣ በስቴት ወይም በብሔራዊ የመንግሥት ሥራ ውስጥ ተቀጥረህ(ሽ) መሥራት ትፈልጋለህ(ሽ)? እንግዲያውስ በዚህ ወር የሚካሄደው "Let's Talk Careers" ለአንተ/ለአንቺ ነው! ዝግጅቱ ረቡዕ፣ ዲሰምበር 16 10–11:30 a.m. እንዲካሄድ መርሃግብር የተያዘለት ሲሆን የመንግሥት መሪዎችም ይሳተፉበታል።

"Let's Talk Careers" በ MCPS ተማሪዎች አማካይነት በየወሩ የሚዘጋጅ እንደመሆኑ፥ ተማሪዎች ከተለያዩ መስኮች ባለሙያዎችን፣ መሪዎችን እና የስራ ፈጣሪዎችን በመጋበዝ ስለሙያ ጉዞ ልምዳቸውን የሚያካፍሉበት ተከታታይ ዝግጅት ነው። ከተማሪዎች የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎችን እንደሚቀበሉ ያረጋገጡልን እንግዶች፦ የሜሪላንድ ስቴት ሴኔተር ቸሪል ኬገን (Maryland State Senator Cheryl Kagan)፣ የሜሪላንድ ስቴት ተወካይ ሊሊይ ኩዊይ (Maryland State Delegate Lily Qi)፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ዋና ኃላፊ ማርክ ኤልሪክ (Montgomery County Executive Marc Elrich)፣ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ካውንስል አባል ሲድኒ ከትዝ (Montgomery County Councilmember Sidney Katz) ናቸው።

ተጨማሪ መረጃ

## የትምህርት ቦርድ በሁለት ፖሊሲዎች ላይ የሕዝብ አስተያየት መቀበል ይፈልጋል

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ **Board Policy JPH የተሰኘ አዲስ ረቂቅ ፖሊሲ ያቀረበ ሲሆን ስለ "School Food and Nutrition Services Programs"** ከአሁን ጀምሮ እስከ ፌብሩወሪ 12/2021 ድረስ የህዝብ አስተያየት እንዲሰጥበት ይፈልጋል። ዲሰምበር 3/2020 ለቦርድ ግምገማ የቀረበው ረቂቅ **እዚህ** ይገኛል።

አዲሱ ረቂቅ ፖሊሲ የተማሪዎችን የመማር፣ የማደግና ጤናን የመጠበቅ አቅም ለመደገፍ MCPS በሞንጎመሪ ካውንቲ የልጅነት ረሃብን ለመቅረፍ በሚደረጉ ጥረቶች አጋር የሚሆንበትን መንገድ በተመለከተ መመሪያ ይሰጣል።

አዲሱ ረቂቅ ፖሊሲ ብቁ የሆኑ ተማሪዎችን በሙሉ በፌደራል ባጀት የሚደገፉ ነፃና የቀላል ዋጋ ምግቦችን (FARMs) ለማመልከት እንዲችሉ ለማበረታታት እና ማናቸውንም የመሸማቀቅ ግርታን ለማስወገድ ወይም ብቁ የሆኑ ተማሪዎችን በሕዝብ ተለይተው እንዳይታወቁ ለመከላከል ለማበረታታትና ለመርዳት የሚደረገውን ጥረት መርሆችንና ስትራቴጂዎችን የሚዘረጋ ነው።

የህዝብ አስተያየቶች **እዚህ** ሊቀርቡ ይችላሉ።

**Policy IQD, Academic Eligibility For Extracurricular Activities**
ቦርዱ ያቀረባቸው ማሻሻያዎች **Board Policy IQD፣ከከሪኩለም ባሻገር ለሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች የአካደሚያዊ ብቃት/Academic Eligibility for Extracurricular Activities** ሲሆኑ፤ እስከ ፌብሩወሪ 12/2021 በማሻሻያዎቹ ላይ የህዝብ አስተያየት እንዲሰጥባቸው ይፈልጋል። ዲስትሪክቱ የፀረ-መድሎ አዊነት፣ ሚዛናዊነት እና ቅቡልነት ያለው ባህል ለማዳበር ባለው ቁርጠኝነት ቦርዱ በስቴት እና በትምህርት ቤቶች መካከል የሚካሄዱ ከከሪኩለም ባሻገር የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች ለብዙ ተማሪዎች ተደራሽ እንዲሆኑ ስፖርቶችን፣ ከትምህርት ሰዓት ውጪ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ የሚጠበቀውን ሚዛናዊነት ለማረጋገጥ ይፈልጋል። የቀረቡት የማሻሻያ ሃሳቦች በርካታ ተማሪዎች በልዩ ልዩ የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ይበልጥ እንዲሳተፉ እና በቀጣይነት የማህበራዊ እና አካደሚያዊ እድገታቸውን እንዲያዳብሩ መርዳትን ታሳቢ ያደርጋል። ኖቬምበር 10/2020 ለቦርድ የቀረበው ሠነድ እዚህ ይገኛል።

ተማሪዎች ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በኋላ በስፖርት ለመቀጠል የሚፈልጉ ከሆነ፥ በስቴት አቀፍ ደረጃ ተማሪዎችን ለአትሌቲክስ ውድድር ለማዘጋጀት እና ለኮሌጅ ደረጃ የሚያበቃ የአካዳሚያዊ ብቃት መስፈርቶችን ለማሟላት እንዲችሉ ለማዘጋጀት በአትሌቲክ እንቅስቃሴዎች ለመሣተፍ የአካደሚያዊ ብቃት መስፈርቶች አስፈላጊ ይሆናሉ።

በትምህርት ቤቶች መካከል በሚካሄዱ የስፖርት ውድድሮች ለሚሳተፉ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት (ሚድል ስኩል) ተማሪዎች የአካደሚያዊ ብቃት መስፈርቶች ለውጥ አልተደረገባቸውም። የሚያስፈልገው አማካይ ውጤት 2.0 ሲሆን በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የሁለተኛ ማርክ መስጫ ክፍለጊዜ ሲጀመር፥ በቀዳሚው የማርክ መስጫ ወቅት ከአንድ በላይ የመውደቂያ ውጤት የሌለው/የሌላት መሆን አለበት።

ቦርዱ ያደረጋቸው ማሻሻያዎች የሚከተሉትን ርእሶች ያካትታል፡-

- ከአካደሚያዊ ትምህርት ባሻገር በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ለሚሳተፉ የመካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በትምህርት ቤቶች መካከል ከሚካሄዱ የስፖርት ውድድሮች በተጨማሪ፥ የተማሪዎች አመራር፣ ስነጥበባት እና የአካደሚያዊ ቡድኖች በመሳሰሉት ላይ ለሚያደርጉት ተሳትፎ የአካደሚያዊ ብቃት መስፈርቶችን በማስወገድ እንዲሳተፉ ይደረጋል።
- በትምህርት ቤቶች መካከል የሚካሄዱ ስፖርታዊ ውድድሮች ላይ ለሚሳተፉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶችን መበየን፣ ከእነዚህ መስፈርቶች አንዳንዶቹ ነፃ እንዲሆኑ ይደረጋል፤ እነዚህም፡-
    - በትምህርት ቤቶች መካከል በሚካሄዱ ስፖርቶች ላይ ለሚሳተፉ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የ 2.0 አማካይ ውጤት መስፈርት ለውጥ አይደረግበትም። ሆንም ግን ባለፈው የማርክ መስጫ ወቅት ከአንድ በላይ የመውደቂያ ውጤት ተቀባይነት አይኖረውም።
    - ይሁን እንጂ ተሻሽለው የሚወጡ የአካደሚያዊ ብቃት መስፈርቶች በሁለተኛው ዓመት በማንኛውም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚጀመሩ ሲሆን ይህም ተማሪው(ዋ) የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በሚጨርሱበት በአራተኛው ሩብ ዓመት ላይ የተወሰነው አማካይ ውጤት ይሆናል።

የህዝብ አስተያየቶችን እዚህ ማቅረብ ይቻላል።

**ቤተሰቦች የአዲስ ዘመን መለወጫ ምግብ በቅድሚያ ማዘዝ ይችላሉ**

ቤተሰቦች ለ 18 ዓመት እና ከዚያ በታች እድሜ ላላቸው ልጆች የአዲስ ዘመን መለወጫ ምግብ በቅድሚያ ማዘዝ ይችላሉ ትእዛዝ ለመስጠት የተሰጠው ቀነ ገደብ እስከ ረቡእ፣ ዲሰምበር 16 ሲሆን ቤተሰቦች ዲሰምበር 29 ከተመደቡ ቦታዎች ምግቦችን መቀበልና ይችላሉ። ለመቀበል ቅድመ ምዝገባ አስፈላጊ ነው።

ትእዛዝዎን እዚህ ይስጡ።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች "ለማርቲን ሉተር ኪንግ (MLK)" ደብዳቤ የመጻፍ ውድድር ተጀምሯል**

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የዶክተር ማርቲን ሉተር ኪንግ "Dear Martin" የተሰኘ የደብዳቤ አጻጻፍ ውድድር ላይ እንዲሳተፉ እናበረታታለን። የ 2021 ጭብጥ ሃሳብ "በእርሱና በእነርሱ አንደበት/ቃላት - ስለ ወደፊት ትንበያ እየታሰበ የቀድሞውን ታሪካችንን መመርመር" የሚል ነው። ተማሪዎች ለዶክተር ማርቲን ሉተር ኪንግ ደብዳቤ እንዲጽፉ ተጠይቀዋል፤ ዶ/ር ኪንግ በሕይወት በነበሩበት ጊዜ ከነበረው ሁኔታ በአሁኑ ወቅት ምን የተለየ ነገር አለ? እና ተማሪዎች ወደፊት ለሰው ልጆች ምን ሲሆን ለማየት እንደሚፈልጉ የሚገልጽ ደብዳቤ ለዶክተር ማርቲን ሉተር ኪንግ እንዲጽፉ ይጠየቃሉ።

የተማሪዎቹ ደብዳቤዎች ለ "ውድ ማርቲን" በሚል የተቀናበሩ እና ቀጥሎ ከተዘረዘሩት የትኩረት አቅጣጫዎች መካከል አንዱን ማለትም ተቃውሞን፣ እኩልነት እና ፍትሕን፣ የመምረጥ መብትን ወይም ስለ አንድነት የማቀንቀን መብትን የሚያንፀባርቁ መሆን አለባቸው። ደብዳቤዎቹ በ 150 ወይም በሚያንስ ቃላት የሚገደቡ ሲሆን ረቡእ፣ ዲሰምበር 23 ከ 11:59 p.m. በፊት መድረስ አለባቸው። ተማሪዎች ደብዳቤዎቻቸውን እዚህ ማቅረብ ይችላሉ።

ጃኑወሪ 18/2021 በካውንቲው ቨርቹወል ለሚከበረው የማርቲን ሉተር ኪንግ መታሰቢያ ክብረ በዓል "MLK Memorial Celebration event" (ከእያንዳንዱ የትኩረት አቅጣጫ) የሚቀርብ ጽሑፍ አራት ተማሪዎች ተመርጠው ደብዳቤዎቻቸውን በንባብ እያሰሙ እንዲቀረጽ ይደረጋል።

ተማሪዎች መስፈርቱን የሚያሟላ ሃሳብ፣ አስተዋይና ትርጉም ያለው ስራን የሚያንጸባርቅ ሥራ ካቀረቡ አንድ የተማሪዎች አገልግሎት መማሪያ (SSL) ሰዓት ማግኘት ይችላሉ። ደብዳቤው የክብረበዓሉ አካል እንዲሆን በቪድኦ እንዲቀረጽ ከተመረጠ፥ ተማሪዎች አንድ ተጨማሪ የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) ሠዓት ያገኛሉ።

ተማሪዎች "በእርሱና በራሳቸው ቃላት - ስለ ወደፊቱ ጊዜ ሲያሰላስሉ የቀድሞ ታሪካችንን በማሰብ" በሚል ርዕስ የተዘጋጀውን የቪዲዮ ፕሮግራም በመመልከት እንዲሁም የማርቲን ሉተር ኪንግ (MLK) ክብረበዓል ሳምንት ፕሮግራም አካል በመሆን ዲስትሪክት አቀፍ የማነቃቂያ እንቅስቃሴ በማድረግ ተጨማሪ የተማሪ አገልግሎት ትምህርት ሰዓቶችን (SSL) ማግኘት ይችላሉ። በ MCPS SSL ድረ-ገጽ ላይ በመጪዎቹ ሣምንታት ይበልጥ ዝርዝር ፖስት ይደረጋል።

**የአየር ንብረት ለውጥ አራማጆችን ለማፍራት የሚደረግ ፉክክር/ውድድር**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ በአየር ንብረት ለውጥ ዕቅድ ውስጥ የሥነ ጥበብ ሥራዎች እንዲካተቱ የሚያደርግ ውድድር እያዘጋጀ ነው። ውድድሩ በሁሉም የዕድሜ ክልል ለሚገኙ ተማሪዎች እና ለካውንቲው ነዋሪዎች ክፍት ነው።

ማኅበረሰቡን ከአየር ንብረት ለውጥ የመጠበቅን አስፈላጊነት የሚያቀነቅኑ ፎቶዎች፣ ሥዕሎች፣ ግጥሞች፣ ቪዲዮዎችና ኦሪጂናል ቀልዶችን ማቅረብ ይችላሉ።

አርቲስቶች ከሚከተሉት ዘርፎች በአንዱ የሥራ ተሣትፎአቸውን ማቅረብ ይችላሉ፦

**ተሳትፎ ማድረግ - መሠማራት!**—በማኅበረሰብና በአየር ንብረት መካከል ያለው ግንኙነት ምንድን ነው?

**የአየር ንብረት አደጋን ማስተጋባት!**—የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትለውን አደጋ በፍጥነት መግታት።

**መላመድ እና መቋቋም** —ማኅበረሰባችን በፍጥነት እየተለወጠ ካለው ዓለም ጋር መላመድ የሚችለው እንዴት ነው?

**አካባቢያዊ/የአየር ንብረት ፍትሃዊነት እና ሚዛናዊነት** —በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚባባሱትን ሁኔታዎች መግታት፤ እንዲሁም በታሪክ የተዳፈኑትን የተጎጂዎችን ድምፅ ማጉላት።

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ የወደፊት ራዕይ** — የግሪንሃውስ ጋዝ ቅነሳ ግቦች አግባብ በሆነ መልኩ ከተሟላ በ 2035 ካውንቲው ምን ሊመስል ይችላል? ይህ ውድድር የወደፊት መልክዓ ምድራዊ አያያዝን፣ የጽንሰ ሐሳብ ስነጥበብ ንድፍ፣ እንዲሁም ሁሉም ነገር የተሟላበት ምናባዊ ቦታ ፈጠራን የሚያበረታታ ነው።

**ቀነ ገደቡ እሁድ፣ ጃኑወሪ 31/2021 ነው።** አሸናፊዎች $100 የሚያገኙ ሲሆን ሥራቸውም በካውንቲው የአየር ንብረት ለውጥ እቅድና በሌሎች ቁሳቁሶች ላይ ሊታይ ይችላል።

የውድድር ደንቦችን ጨምሮ ተጨማሪ መረጃዎች እዚህ ይገኛሉ።